# ትንቢተ አብድዩ (48)

## አብድዩ 1፡1-21

የጥናት ዓላማ፡- እኛ በወንድሞቻችን ላይ የምንፈጽመው በደልና ግፍ በእግዚአብሄር አምላካችን ፊት አጸያፊ እንደሆነ ግልጽ ቢሆንም እንኳን፤ ሌሎች ሰዎች በወንድሞቻችን ላይ የማይገባ ነገር ሲያደርጉ እያየን በገለልተኛነት ዝም ብለን ማሳለፋችንም በፊቱ ሐጥያት እንደሆነ ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እንግዶች ሃብቱን ዘርፈው ሲወስዱ፣ ባዕዳን በበሮቹ ሲገቡ፣ በኢየሩሳሌም ላይ እጣ ሲጣጣሉ፣ በዚያ ቀን ገለልተኛ ሆነህ ተመለከትህ፣ አንተም ከእነርሱ እንደ አንዱ ሆንህ።" አብድዩ 1፡11

1. ትንቢተ አብድዩ 1፡1-21 በአንድነት ይነበብ፡፡ ነብዩ አብድዩ ትንቢቱን ያተኮረው በማን ላይ ነው? ዘፍ 25፡30ንና ትንቢተ አብድዩ ቁ10ርን በመመልከት በዚህ ስም ስለሚጠራው ሰው ወይም ህዝብ ማንነት ማወቅ የምንችለው ነገር ምን አለ?
2. ቁ2-4ትን ስናነብ እግዚአብሄር በዚህ ህዝብ ላይ በፍርድ መልክ ሊያደርግ ያሰባቸው ቢያንስ ሶስት ነገሮችን እንመለከታለን፤ እነዚህ ሶስት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። ይህንን ክፍል በትኩረት ስንመለከት፣ እግዚአብሄር በዚህ ህዝብ ላይ እነዚህን የመሳሰሉ የፍርድ አነጋገሮችን ሊናገር የቻለበት ዋነኛ ምክንያት አድርጎ የሚናገረው ነገር ምንድነው?
3. ቁ5-6 ላይ የኤዶምን ጥፋት ከሁለት ሁኔታዎች ጋራ በማነጻጸር ይናገራል፤ እነዚህ ሁለት ከኤዶም ጥፋት ጋራ የሚያነጻጸራቸው ነገሮች ምንና ምንድናቸው? በነዚህ በሁለት ቁጥሮች የሰፈሩትን ሃሳቦች ብቻ በመመልከት፣ እነዚህን ሁለት ማነጻጸሪያ ሃሳቦች በማምጣት ነብዩ ስለ ኤዶም ጥፋት ሊያስረዳ የፈለገው ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
4. ቁ7-10 ላይ ነብዩ አብድዩ በኤዶም ላይ ስለሚነሱ ሶስት አይነት ሰዎችና ድርጊታቸው ምን እንደሚሆን ይነግረናል። እነዚህ ሰዎች እነማን እንደሆኑና ድርጊታቸው ደግሞ ምን ምን እንደሚሆን በመዘርዘር ተናገር። ይህንን ክፍል ስታነብ እግዚአብሄር በኤዶም ላይ እንደዚህ ያለውን ከባድ ነገር እንዲያደርግና ለዘለዓለም ሊያጠፋት እስከመወሰን ድረስ ያደረሰው ነገር ምንድነው? ዘሁልቁ 20፡14-21ድን ስናይ ይህ ኤዶም በወንድሙ በያዕቆብ ላይ ካደረጋቸው የግፍ ድርጊቶች ስለየትኛው ነው የሚነግረን? አንተስ ወንድምህ እንዳያድግና እግዚአብሄር ሊደርስ ከሚፈልግበት ግብ እንዳይደርስ እንቅፋት ያኖርክበትን ጊዜ ታስታውሳለህ ወይ?
5. በቁ11-14ትን ስትመለከት ኤዶም በወንደሙ በያዕቆብ ላይ እንዳደረገ የተነገረን ነገር በየቁጥሩ ላይ እየጨመረ ሲሄድ ነው የምናየው። ከቁ11-14 በያንዳንዱ ቁጥር ውስጥ ሃጥያቱ እንዴት እየከፋ እንደሄደ አስረዳ። ትንሽ የሚመስለው ሃጥያት እያደረ ሲሄድ ምን ያህል አስከፊና አደገኛ ህይወት ውስጥ ሊያስገባህ እንዲችል ምን ያህል ተገንዝበሃል?
6. ቁ15-16 ላይ ስናይ የእግዚአብሄር ፍርድ ትክክልና ያልተዛባ እንደሆነ ሊያስረዳን የሚችል አነጋገር እንመለከታለን፤ ይህንን በየትኛው ቁጥር ውስጥ እንደምናገኘውና ምን እንደሚልም ጭምር ተናገር። ይህንኑ የመሰለ አነጋገር በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሰፍሮ እናገኛለን፤ ከአዲስ ኪዳን ይህንን ሃሳብ በሚመስል መንገድ የተነገረና የምታስታውሰው ሃሳብ ካለ ለወገኖች ተናገር።
7. ቁ17-21 እግዚአብሄር ከእርሱ ጋራ የሆነና እርሱ የሚዋጋለትን ህዝብ መጨረሻ ያሳያል። በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ለያዕቆብ ሊሆንለት እንዳለ ከተነገሩት ነገሮች መሃል ጥቂቶቹን ዘርዝር። ይህ ሁሉ በምድር የሚካሄደው ግርግር ካበቃ በኋላ ሊሆን ስላለው ነገር ወይም የነገር ሁሉ መደምደሚያ ይሆናል በሎ ጸሐፊው የሚናገረው ነገር ምንድነው?
8. በቁ11 ላይ ተመልሰን ስንመለከት የኤዶም ሐጥያት ምን እንደነበረ ነው የምንመለከተው? አንተስ በወንድምህ መከራና ችግር ጊዜ በምን አገባኝነት ከዳር ቆመህ ትመለከታለህ ወይስ በምትችለው ሁሉ ከጎኑ ለመቆም ትሞክራለህ? እንደ አንድ አባት ልጆች እኛም ወንድማችን ወይም እህታችን የሚያልፉበትን መከራ የራሳችን እንደሆነ ቆጥረን ከጎናቸው በመቆም የምንችለውን ሁሉ የማድረግ ሃላፊነት እንዳለበን መዘንጋት አይገባንም።